# ፖለቲካን ከፕሮፖጋንዳ የማይለዩ ….. ፫

**ዮናስ 07/04/14**

የሃገሬን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስልታዊና ስትራቴጂካዊ መመሳቀል ለማሳየትና ለመመሳቀላቸውም መነሻው የበዛ ቢሆንም፤ በዋናነት ግን ፖለቲካን ከፕሮፖጋንዳ አለመለየታቸው እንደሆነ ሁለተኛ መነፅራችንን ከህወሃቱ መስራች አቶ አሰገደ ገ/ሥላሴ ተውሰን ክፍል ሁለት ምልከታችንን መነፅር አዋሻችን ከሆኑት አቶ አሰገደ መነሻዎች ማድረጋችን ይታወሳል፡፡ ይኸውም ‹‹ውስጣዊ ጥራት ለተቃዋሚ ፓርቲዎች›› በሚል አቶ አሰገደ በኢትዮ ምህዳር ቅፅ 02 ቁጥር 73 ላይ ያሰፈሩት ፅሁፍ አህያውን ፈርቶ ዳውላውን እንደሆነባቸውና ለተቃዋሚዎቹ ህፀፅ ህወሃትንና ኢህአዴግን ተጠያቂ ናቸው ብለው የባሰው አዘቅት ውስጥ ነከሯቸው፤ የተነከሩባቸውን ነጥቦች መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን እና በተለይ ከመገንጠል፤ ከዴሞክራሲያዊና ከመሳሰሉቱ ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ ህወሃትን እንደ ብሄራዊ ድርጅት፤ ግንባሩንም እንደገዢ ፓርቲ ለማንኳሰስ ይረዷቸው ዘንድ ላነሷቸው ነጥቦች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

በዚህ ክፍል ደግሞ ህወሃትን እና ገዢ ስርዓቱን የወረዱባቸው መንገድ ትክክል እንዳልነበር ይልቁንም ፀረ ዴሞክራሲያዊ እንደነበር እራሳቸው ከተቃዋሚ ፓርቲዎች አንፃር ካስቀመጧቸውና ነጥቦቹም የእራሳቸውም መገለጫ እንደሆኑ  የምንመለከት ሲሆን ይልቁንም ለነህወሃትና ግንባሩ የለጠፉላቸው ታፔላ የራሳቸው እንደሆነ ከእርሳቸው የምስክርነት ቃል ጋር እያንሰላሰልን እናያለን፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በውስጠ - ዴሞክራሲ ህይወትና ጥራት ቦታ ሰጥተው የአንድነትና የትግል ጉዞን አቅጣጫ ተከትለው እንደማይጓዙ የሚገልፁት አቶ አሰገደ ይኸው ጉዞ ለውድቀት እንደዳረጋቸው ተረድተው እና ተምረው ያኗቸውን መሰረታዊ ያልሆኑ

ልዩነቶች በማጥበብ ለአንድነትና **ለውህዷ ኢትዮጵያ** እየተጋለ እንዳልሆኑ ይመሰክራሉ፡፡ በእርግጥ ይህ ምስክርነት ውህዷ ኢትዮጵያ የተባለችውን በክፍል 2 ላይ ባነበርነው አግባብ ተረድተን መሰረታዊ ያልሆኑ ልዩነቶች የሚለውን ገለፃቸውንም ወደኋላ ከምንመለከተው ትንታኔ አንፃር የሚቃኝ መሆኑን ታሳቢ አድርገን ምስክርነታቸውን ትክክል ነው ብለን እንቀበላለን፡፡ ችግሩ ግን ውህዷ ኢትዮጵያን እንድንረዳቸው በተመለከተው እና መሰረታዊ ያልሆኑ ልዩነቶች ያሏቸውን የተቃውሞውን ጎራ ቅኝት ይዘን እውነታውን ብንቀበላቸውም አቶ አሰገደ ቀደም ብዬም እንዳልኩት አዙሪት ውስጥ ሆነውና ከአዙሪት ለመውጣት ሳይዳዱ ለመምከር መሻታቸው ተገቢነት የሌለው እንደሆነ የሚያሳይ ነጥብ ያነሳሉ፡፡

ከላይ የተመለከተውና አቶ አሰገደ ስለተቃዋሚዎቹ የሰጡት የምስክርነት ቃል ምንጩ የተቀዋሚዎቹ ሳይሆን ከህወሃት፣ ኢህአፓና ኦነግ የተወሰዱ ተሞሮክዎች እንደሆኑና ይልቁንም የተቃዋሚዎቹ አንጡራ ችግሮች የህወሃት ኢህአዴግ መሪዎች ሌጋሲ እንደሆኑ ማንሳታቸው ነው የአልሸሹም ዞር አሉ ምክራቸውን አዘቅት የሚከተው፡፡

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ነባር ይሁኑ አዲሶቹ በውስጣቸው *በስብሰው* እያሉ ራሳቸው ‹‹በጥሩ ሁኔታ አለን›› የሚሉ ቢሆንም በውስጣቸው ጥሩ ያልሆኑ ፓርቲዎች፣ በውስጣቸው ለሚነሱ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ‹‹የጥያቄዎቹ መንስኤ ምንድናቸው? ከየትኛው አቅጣጫ ነው የተነሱት? ውስጣችንን እስኪ እንፈትሽ?›› ብለው ለራሳቸው ቅድሚያ፤ በኋላም ለአባሎቻቸው እና ለደጋፊዎቻቸው መድረክ ከፍተው እንደመገማገም ፋንታ በአንፃሩ ጥያቄ ያነሱ የአባሎቻቸውን ስም በማጥፋት ‹‹የህወሃት ኢህአዴግ ቅጥረኞች፣ የተገዙ፣ ከጂዎች›› እያሉ በአሽሙር በብዙሃን መገናኛ፣ በማህበራዊ ሚዲያ (ፌስ ቡክ) እየተሳደቡ ይገኛሉ፡፡›› ሲሉ አቶ አሰገደ ይገልፃሉ፡፡

በእርግጥም በክፍል አንድና ሁለት ላይ ከዴሞክራሲና ከዴሞክራሲያዊ ስርዓት ጋር ተያይይዘው በቀረቡት መከራከሪያዎች አግባብ የአቶ አሰገደ ከላይ የተመለከተው ምዘና ትክክል ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ተቃዋዎቹ የሚገለፁበትና ከላይ የተመለከተው ህፀፅ አቶ አሰግድ አስቀድመው የህወሃት ተሞክሮ እና ሌጋሲ ነው ብለው ለጥፈውባቸው ሲያበቁ መልሰው ‹‹ጥያቄ የሚያነሱ አባሎቻቸውን የህወሃት ኢህአዴግ ቅጥረኞች፤ የተገዙ ገዥዎች እያሉ ይዘልፋሉ›› ብለው ማንሳታቸው ተገቢነት የሌለውና ለራስ የማይሹትን ለሌላውም ካለመሻት ሞራላዊ ተጠየቅ ጋር የሚላተም ግምገማ ነው፡፡ በእርግጥ ከአቶ አሰገደ ገለፃ እንደተረዳነው ዘለፋው የደረሰው በብዙዎች ላይ ቢሆንም በእርሳቸው አቀራረብ እራሳቸውን የተመለከተ እና በአባሎች አስመስሎ የቀረበ ነቀራ ቢሆንም አስቀድመው በነቀፉበት አግባብ ማንቀራቸው አይገርምም፡፡

ይህ ጉዳይ አግራሞት የሚያጭርብን ሌላኛው ምክንያት ለዚህና በተቃዋሚዎቹ ላይ ለቀረበው የዘለፋ ክስ መነሻው ህወሃት ነው ሲሉ በድፍረት መናገራቸው ነው፡፡ ከላይ ለተመለከተው የአቶ አሰገደ ክስ መንደርደሪያው ምን ይል መሰላችሁ? ‹‹.. ህወሃት ውስጠ ብስባሴውን (በአንድ ወቅት የህወሃት ኢህአዴግ ሊቀመንበር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊም ፓርቲው በውስጡ መበስበሱን እንደተናገሩ ልብ ይሏል) ደብቆ፣ ውጫዊ ገፅታውን እንዲሸፍን ተጠቅሞ ታጋዩ እና ህዝቡ ለውስጠ ትግል ቦታ እንዳይሰጡት በማጭበርበር ይጓዝ እንደነበረው ሁሉ ….” የሚል መንደርደሪያ፡፡

በእርግጥ ከዴሞክራሲያዊና ውስጣዊ ትግሎች አኳያ በተለይ በክፍል ሁለት ትርክታችን በሚገባ የተብራራ ቢሆንም አቶ አሰገደ ችግራቸውን ትተው የህወሃት ቅጥረኛ ይላሉ የሚለውን ክስ ከማቅረባቸው አስቀድመው ተቃዋሚዎቹን “የህወሃት ሌጋሲ አስቀጣዮች” ብለው ፈርጀዋልና ነገርዬው እንደ ፖለቲካ ከሳሽም ሆነ ተከሳሾች ያውና በተደጋጋሚ

እንደተገለፀው  ፀረዴሞክራሲያዊ ቢሆኑም በሞራላዊ ተጠየቅ አግባብነት እንኳ ብናሂሰው እሾህን በሾህ ነውና አቶ አሰገደ ከተቃዋሚዎቹ በላይ ውስጣዊ ጥራት የጎደለው አመለካከታቸውን ይፈትሹ ዘንድ ልንመክራቸው እንገደዳለን፡፡

አቶ አሰገደ ሲቀጥሉም በጥቅል የከሰሷቸውን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለይተው በኦሮሞ ፓርቲዎች፣ በአንድነት፣ በአረና ትግራይ ፣ በመኢአድ፣ በደቡብ ህብረት፣ በሰማያዊ ፓርቲና ሌሎች ብለው ይጠቅሳሉ፡፡ እነዚህን የተለዩና በስም የተጠቀሱ ፓርቲዎች መሪዎች ፈላጭ ቆራጭነት ስልጣናቸውን እንዳይነጠቁ የሚያሰጋቸው እንደሆነ፣ የኢትዮጵያ አውራ ፓርቲ አምባገነን ለመሆን የሚሰሩ እንደሆነ፣ በተለይ ብለው አንዳንዶቹ ፊፅሞ የተማረ ሰው የማያስበውን የሚያደርጉ፣ በጨቅላ አስተሳሰብ እና በግብታዊነት ላይና ታች የሚሉ እንደሆኑ ገልፀው ከድርጊታቸውም እንዲቆጠቡ ያሳስባሉ፡፡ በእርግጥ ግባቸውን የህዝበ ተወካዮች ም/ቤት አድርገው የደንባራ በቅሎ ጉዞን እንደሚከተሉና በዚያም ላይ ያልሰሩትን ፖለቲካ በፕሮፖጋንዳ ለማጀብ መሻታቸው ቃጭል ተጨምሮ አይነት እንደሆነ በተደጋጋሚ መግለጻችን ትክክል እንደነበር ይህ የአቶ አሰገደ ግምገማ ዋቢ ይሆነናል፡፡ ያም ሆኖ ግን አቶ አሰገደም ከደንባራይቱ በቅሎ ያልተለዩ እንደሆኑ በራሳቸው ራሳቸው ላይ ሊሰመክሩልን ከላይ በተመለከተው በስም የተጠቀሱት ተቃዋሚዎች ላይ የቀረበው ክስ የተቃዋሚዎቹ የራሳቸው ሳይሆን "ከህወሃት የተወረሰና ይልቁንም ፀረውህዴ አንድነቷ እና ሉዓላዊነቷ የተጠበቀች ኢትዮጵያን እንዳትኖር የህወሃት ኢህአዴግን ፍላጎት ለማሟላት የሚደረግ ድርጊት ነው›› በማለት ነው፡፡ ይህ እንግዲህ እራሳቸው ከፍረጃ ሳይወጡ ለምን ተፈረጅን ማለታቸው በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ ስለመሆኑና ፍረጃን በፍረጃ ለማሂስ መሻታቸው ደግሞ እንደፈረጇቸው ተቃዋሚዎች የጨቅላ አስተሳሰብ ውጤትና በግብታዊነት የታጨቀ ክስ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ተቃዋሚዎቹም ሆኑ አቶ አሰገደ እራሳቸው ግባቸው ስልጣንና ዝና መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንንም ለማጠየቅ በፀሃፊው በኩል የቀረቡት አብነቶች ሁሉ መንስኤው ህወሃት ነው ተብሎና ከህወሃት ጋር ተንሰላስሎ መቅረቡን ሳንዘነጋ፣ በአናቱም ችግሩ የራሳቸው አጀንዳ የህወሃት ኢህአዴግ (ከሳቸው ክስ አንፃር) ማንነት በክፍል ሁለት ላይ በሚገባ መብራቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዋና ዋና የሆኑትን እና በአቶ አሰገደ በኩል ከቀረቡት ተቃዋሚዎቹን የተመለከቱቱ ማንነቶች የተወሰኑትን አንስተን ወደ ሌላኛው ማጠየቂያ መነፅራችን እንሻገራለን፡፡

ተቃዋዎቹ በተለይም ከላይ በፀሃፊው ስማቸው የተጠቀሱቱ የክልሎቻቸው እና ብሄራቸው ንጉሶች በመሆን በኪሳቸው የዘውድ አክሊልን ለመድፋት እንዲሁም ዘውድን ለመስቀል (በመግዛት) ለውስጠ ዴሞክራሲ እንቅፋት ስለመሆናቸው ከአቶ አሰገደ ቀድመን እኛም ብለን እንደነበር ይቆጠርልን፡፡

እነዚህ ፓርቲዎችና አመራቻቸው በውስጣቸው ለሚነሱ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች በስክነት አዳምጠው መልስ መስጠትን የማያውቁ እና የማይሹ ይልቁንም አየር ላይ ተንሳፈው በኢነተርኔት ፌስ ቡክና ጋዜጦች መግለጫ ለመስጠት የሚሮጡ መሆናቸውንም አቶ አሰገደ ቢነግሩንምና ትክክል ቢሆንም ፖለቲካን ከፕሮፖጋንዳ የማይለዩ ብለን አስቀድመን መናገራችንም እንዲሰመርልን እንሻለን፡፡

*ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ አንስተው በፓርቲዎቹ ውስጥ የሚከሰቱ ስህተቶችን ለማስተካከል ባለመቻላቸው ከትግሉ ራሳቸውን ሲያገሉ በእነርሱ ፋንታ የሚተኩ አመራሮች ወደነበሩበት አላማ እንዲመለሱ ማበረታታት ሲገባቸው ይባስ ብለው ሰብአዊ መብታቸውን ይነካሉ* የሚለውም የአቶ አሰገደ የምስክርነት ቃል (እኛም ያልነውና የነበረ እውነታ መሆኑ እንደጠበቀ ሆኖ) ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ የሚለውንም አገርኛ ብሂል አቶ አሰገደ

ቢያስታውሱት በተቃዋዎቹ ላይ ያወረዱት እውነት የእርሳቸውም መገለጫ እና ማንነት እንደሆነ በተረዱት ነበር ስንል ለማስቆጠር እንገደዳለን፡፡ በመጨረሻም ህወሃት ኢህአዴግን ‹‹አውራ ፓርቲ›› ነኝ›› ‹‹ማን እንደ እኔ›› በማለት ቁም ስቅሉን በየፌስቡክና ጋዜጦቹ ሲያሳዩ የነበሩት፤ እያሳዩም የሚገኙት አቶ አሰገደ እርሳቸውም ይህን የተቃዋሚዎቹ ጋዜጣዊ መግለጫና ፌስ ቡክ … እንዳላሉ ሁሉ በጋዜጣ እየዘለፏቸው መሆናቸው እደተጠበቀ ሆኖ፤ በሃገራችን ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተናጥል ‹‹እኔ ነኝ አውራ ፓርቲ›› እያሉ ከመበጣበጥ ይታቀቡ›› በሚል ምክር አዘል አስተያየት ፅሁፋቸውን መደምደማቸውም፡፡ ከህወሃት ኢህአዴግ ሳይሆን የአውራ ፓርቲነት ፍላጎቱም ሆነ ምኞቱ እስከመበጣበጥ የደረሰ ደረጃ ላይ የሚገኘው ተቃዋሚዎቹ ቤት መሆኑን አፅንኦት ሰጥተን እንድናሰምርበት እድሉን ከመስጠትም አልፎ ብለን ከነበረው ሁሉ ከፍ ያለም ፀረዴሞክራሲያዊ የተቃዋሚዎች መገለጫ እንዳለ ያመላከተን ነው፡፡

ቀድሞም ቢሆን የአንድነት ፍንካች መሆኑ የሚታወቅ ሆኖ ሳለ ለምን ሲሉ ስለውህደት እንደሚያሂሱት ባይገባኝም፤ ይህ የገባውና የውህደትን የተደበቀ አጀንዳ የተረዳ የሚመስለው ሰማያዊ ፓርቲ ወይም በራሱ ምክንያት ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ትብብር እንጂ ውህደት ጂኒ ቁልቋል የማይሻ መሆኑን በተደጋጋሚ በመግለፅና በዚህም ከተለያዩ ፓርቲዎች ውርጅብኝ ሲደርስበት የነበረ መሆኑ የሚታወስና እኛም በክፍል አንድ እና ሁለት መጣጥፋችን ላይ የተመለከትነው መሆኑ ይታወሳል፡፡

ይህን ተከትሎ ታዲያ ብርሃኑ ተክለ ያሬድ የተባለ የሠማያዊ ፓርቲ የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ በ*ኢትዮ ምህዳር* (ግንቦት 27 ዕትም) ጋዜጣ ሰማያዊ ፓርቲ ውህደትን የማይሻበትን እና ትብብርን የመረጠበትን ምክንያት የተመለከተ ሀሳብ ይሰጣል፡፡ ሃሳቡ ከጉዳዩ ጋር የተያያዘ ነው? ሠማያዊ ፓርቲ ውህደትን የማይሻበት ምክንያቶችስ ትክክል ነበሩ ወይስ

አይደለም? የሚሉት ነጥቦች ጉዳያችን አይደሉም፡፡ ዋናው ጉዳያችን የአቶ ብርሃኑን የግንቦት 27 ሰማያዊ ፓርቲን የተመለከተ ሀሳብ፤ በሃሳብ ለመምታት የቀረበውና በሰኔ 18 ቀን 2006 በኢትዮ ምህዳር ጋዜጣ ላይ የሰፈረው የአቶ ግርማ በቀለ ሃሳብ ነው፡፡

አቶ ግርማ በቀለ ለበርካታ ዓመታት  በተቃዋሚው የፖለቲካ ጎራ ተሰልፈው የነበሩ እና የተለያዩ ፓርቲዎችንም በአመራርነትና በአባልነት ያገለገሉ ከመሆናቸው አኳያ አሁን ላይ ደግሞ የ33ቱ (ተፈረካክሰው አስራዎች የሆኑት) የፓርቲዎች ጥምረት ዋና ጸሀፊና የትብብር ለዲሞክራሲያዊነት ኢትዮጵያ ትብብር ሊቀመንበር ከመሆናቸው አንጻር መነሻቸው ምንም ይሁን ምን ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በተመለከተ የሚሰጧቸው አስተያየቶች፤ ምልከታዎች (እርሳቸውንም የሚያካትት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) ከመሬት ጠብ የሚል አይመስለኝም፡፡ ከ1986 ዓ. ም (የአማራጭ ሃይሎች ም/ቤት ምስረታ) እስከዛሬ (ትብብር) በተደረጉ አብሮ የመስራት ጥረቶች ሁሉ (33 የተባሉትንም የሚጨምር እንደሆነ ያጤኗል) በአብዛኞቹ ትብብሮች በአመራር ደረጃ መስራታቸውና ከልምዳቸውም ተቃዋሚዎችን በተመለከተ አለ የሚሉት ችግር ያሚያስቀምጡት አቶ ግርማ በቀለ እንዲህ ሲሉ ነው፡-

*…በትብብርም ሆነ ግንባር ለመስራት ውህደትም ለመፈጸም መሰረታዊ ችግሩ ከፓርቲዎች የዓለማና የአፈጻጸም ልዩነት በእጅጉ በላቀ «የፓርቲ መሪዎች ስልጣን ላለማጣት» የራሳቸውን ኪስ  እና የግል ፍላጎት ከአገር ጥቅም በላይ አድርገው በመመልከት በሴራ ፖለቲካ የተጠመዱ በፓርቲ ጥቅም ማስከበር ስም የሚያቀርቡት ውሃ የማያነሳ ምክንያት ነው፡፡*

ይህ እንግዲህ ከራሳቸው ትብብርና ውህደትን ሲመሩ ከነበሩ ጉምቱ የፖለቲካ ሰው የተነገረና ተቃዋሚዎቹን የተመለከተ እይታ ነው፡፡ የኪስ ዘውድና ዝናን ለማትረፍ የሚንቀሳቀሱ እና የሚሰሩ ሀይሎች ባልሰሩት ፖለቲካ ተደርጎ እንኳ ቢሆን ምህዳር ጠበበ፤ አባላቶቼ ታሰሩ ጂኒ ቁልቋል ሲሉ ፕሮፖጋንዳቸውን ቢነዙ በምን ሂሳብ ልናወራ ርድላቸው ሽተው እንደሆነ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል እነዚህ በፕሮፖጋዳና በመግለጫ ታጅበው ያለአንዳች የፖለቲካ ስራ በሰላማዊ ሰልፍ አብደው የሚያሳብዱ ሃይሎችን በተመለከተ እኚህ ላለፉት 20 አመታት ስለ ውህደትና ትብብር አመራር በመሆን የሰሩትና የልምድ ባለቤት የሆኑት ግለሰብ ተቃዋሚዎቹን በተመለከተ ገዢው ፓርቲ ከሚገልፃቸውም በላይ ማንነታቸውን እንዲህ ሲሉ ቁልጭ አድርገው ያመላክቱናል፡፡

‹‹…. ዛሬ ላይ ለምናየው የውህደት ችግር ሆነው ለሚቀርቡ ምክንያቶች ወደየፓርቲያችን ውስጥ እና ወደመሪዎቹ የ‹‹ኢጓምካሽን›› ሠለባነት ደረጃ መመልከትና የፓርቲዬ ጥቅም አልተጠበቀም፣ አመራሩን ማን መያዝ አለበት/ይችላል፣ (እስቲ አስቡት በአደጋ ላይ ናት በሚኋት አገር፣ በህዝቡ የሚደርሰው ስቃይና አድልኦ ከሸክሙ በላይ ነው በሚሉበት የየቱ ወይም የትኛው ፓርቲ ጥቅም ነው የሚከበረው? የትኛው አመራር ነው የተናጥል መፍትሄ ያለው? የትኛውስ ፓርቲና መሪ ነው በአገር ላይ ከተደቀነው አደጋና በህዝብ ላይ ከሚደርሰው ሰቆቃ በላይ የሆነው? …) ወዘተ የሚሉ ተራ ጉዳዮችን በየመግለጫውና ሰላማዊ ሰልፉ ከሚገልፁት አገራችንና ህዝቧ ከፊታቸው ተደቅኗል ከሚሉቱ ፈታኝና አደገኛ ሁኔታ እንዲሁም ከሚያሰሙት የሰቆቃ ድምፅ/መፈክር አንፃር እንዲመዝኑት ማስገደድ እንጂ ‹‹የእምዬ መቀነት ጠለፈኝ›› በምንም መከራከሪያ ለየቱም ፓርቲና የፓርቲ አመራር/መሪ መሸፈኛ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡››

ከዚህ በላይ ለያዝነው ርዕሰ ጉዳይ መገለጫ ከወዴት ይገኛል ጃል?፡፡ ህዝቡና ሀገሪቷ አደጋ ላይ መሆናቸው እና አለመሆናቸው እነርሱ ስላሉ ናቸው ብለን ለመደምደም ቢቸግርም ሆኖ እንኳን ቢሆን፤ ሸክሙም ከብዶን እንኳ ቢሆን፤ ሸክማችንን ሊያቀሉ ከአደጋውም ሊያተርፉን በስማችን የተቋቋሙት ፓርቲዎች እንግዲህ እንዲህ ሰውዬው የገለጿቸው እና በሰላማዊ ሰልፉና መግለጫ ሰቆቃ ከማሰማት ያልተቸገሩቱ ናቸው፡፡ ሰውዬው

እንደገልፁልን ያለአንዳች የፖለቲካ ስራ በፕሮፖጋንዳ መጠመዳቸውም ሲያጋልጣቸው ‹‹የእምዬ መቀነት ጠለፈኝ›› በማለት ገዢው ስርዓት ላይ ለማላከክ የሚፍጨረጨሩበት አግባብ በምንም መመዘኛ ትክክል እንዳልሆነ እራሳቸው የእነርሱ ጓድ መስክረውልናል፡፡ ምርጫ 2007ን መሰረት በማድረግ ባልሰሩት ፖለቲካ በፕሮፖጋንዳ የሚያደነቁሩንን ፓርቲዎች በተመለከተ ከክፍል አንድ እስከ ሶስት ለመቃኘት የሞከርንበትን እና የያዝነውን ጭብጥ የምንጠቀልለው በዚህና ከላይ የተመለከቱ ሃሳቦችን ስለ ተቃዋሚው ሃይልና ግርግር በነገሩን ግለሰብ የማጠቃለያ ሀሳብ ነው፡፡ ለምን ቢሉኝ ነበሩበትና በደንብ የሚያውቋቸውን ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንኳንስ ስላለፈው ወደፊታቸውንም በሚገባ ገልፀውልናልና ነው፡፡ መጠቅለያቸውም ሀሳብ ሳይሆን ብለው ብለው ያቃታቸውና የተዋቸው መሆኑን የሚሳብቅ ምልጃ ነው፡፡ (ምንም እንኳን ምልጃው እርሳቸውም ስለተነኩ የተፃፈ ቢሆንም ቁምነገሩ ስለተቃውሞ ፖለቲካ ያልነውና ተናግረን የነበረው ሁሉ ትክክል እንደነበር ማሳየቱ ነው)

*መተባበር ቢያቅተን መከባበርና የየራሳችን የቤት ስራ ላይ ትኩረት በማድረግ በመናቆር የምናባክነውን ሀብት እንቆጥብ፤ የምናወራውና የምንሰራው ስለአንድ ሃገር መሆኑን ሁሌም ለማስታወስ እንሞክር፡፡ እባካችሁ በባዶ ፕሮፖጋንዳ ለህዝብ የተስፋ ዳቦ ከማቅረብ በዘላቂ አገራዊና ህዝባዊ ጉዳይ ላይ ተጨባጭ ተግባር ለማከናወን ፓርቲያችንን ከተቻለን በጋራ እንምከር፤ ካልተቻለንም በራሳችን ስራ ላይ እናተኩር፡፡*

ሰውየው ይቀጥላሉ፤ ልብ በሉ አንጋፋው የተቃዋሚዎች ፓርቲ ጥምረት አስተባባሪና በተቃውሞ ፖለቲካውና በማስተባበሩ ስራ የረዥም ጊዜ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው ሰው ናቸው፡፡ እንዲህ ሲሉ የወደፊቱንም ተስፋ የተጣለበትን እና ፕሮፖጋንዳ እየተነዛበት የሚገኘውን ምርጫ 2007 በተመለከተ ‹‹እዚህ ላይ መቼም እና ማንም ይሁን በተናጠል ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሚመጥንና ከገባንበት አዘቅት የሚያወጣን የተቃዋሚ ፓርቲ ዛሬ ላይ የለም ብዬ እንደማምን፣ ወደፊትም አሁን በፖለቲካው መድረክ ላይ ያሉት

ከተወሰኑ ፓርቲዎች እየተገነጣጠሉ በተመሳሳይ የአስተሳሰብ መዋቅር ላይ የተመሰረቱ፣ ከራሳቸው የቤት ስራ በላይ ሌላውን ለማሳነስ የሚተጉ፣ ፕሮፖጋንዳን ከፖለቲካ የማይለዩ፣ በመጠላለፍና መወነጃጀል ላይ የሰለጠኑ፣ በዲያስፖራ ድጋፍ በመመካት ለመራጩ ህዝብ ክብር የማይሰጡ፣ ቦታውን ሳይለቁ ወይም ከታሪክ ተምረው ወደ አገራዊ አስተሳሰብ ሳይመለሱ አገሪቱ የምትፈልገውንና ህዝቡ የሚጠብቀው ዲሞክራሲያዊ የተቃዋሚ ፓርቲ ስለመፈጠሩ በእጅጉ እጠራጠራለሁ፡፡”

የኛም አቋምና ጥርጣሬ ይኸው ነው፡፡